@BOOKALEM

የመጻሕፍት አለም

# የሺ ሀረጊቱ

በአንጋፋው አርቲስት ማሕሙድ አህመድ
ሙዚቃ መነሻነት የተጻፈ




በደጀኔ ተሰማ

ወጥ
ልብ ወለ

@B

ሸር 0041

# የሺ ሐረጊቱ

## ወጥ ልብ ወለድ

በ ደጀኔ ተሰማ

2005 ዓ.ም

@BOOKALEM

© ደጀኔ ተሰማ 2005 ዓ.ም አዲስ አበባ

በመጽሐፉ ላይ ያለዎትን አስተያየት በሚከተለው አድራሻ ያሳውቁን
+251 911 044765 E-mail yeshiharegitunovel@gmail.com

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ሐምሌ 2005 ዓ.ም
አታፍዘር ማተሚያ ቤት ታተመ

---

የውስጥ ገጽ ዲዛይን፡- ስለሺ ሁነስ
ሽፋን ገጽ ዲዛይን፡- አርታኢ ስቱዲዮ 0911687256

# ምስጋና

- የሺ ሀረትጊቱ የተሰኘችው ይህች መጽሐፍ በየሺ ሀርጊቱ ሙዚቃ ውስጥ ተፀንሳ ከዓመታት ምጥ በኋላ እነሆ ተወልዳለች፡፡ ለዚህ መነቃቃት ምክንያት ለሆነኝ ለሙዚቃው ጌታ ለአንጋፋው አርቲስት መሀሙድ አህመድ ታላቅ ምስጋናዬን ይድረስ ብያለሁ ፡፡

- ከምንም በላይ እናንተ ውድ የሆናችሁ ወዳጆቼ ለህልሜ ታማኝ ሆኜ እሩቅ አልሜ ለመድረስ የዕራይን መኪና ሳሽከረክር በጉዞዬ ላይ ጎማው ተበላሽቶ ልቆም ባልኩበት ጊዜ ጎማ የቀየራችሁልኝ ፤ በጎዞው ረኸምኑት የተነሳ ነዳጅ ጨርሼ ስንገራገጭ ነዳጅ ሆናችሁ መንገዴን ያስቀጠላችሁኝ ፤ የጉዞዬ መዳረሻ ረዝሞ ታከቶኝ ተስፋ ለመቁረጥ ስዳዳ ብርታት ለሆናችሁኝ ቢኒያም ዮሐንስ፣ መብራቱ ቱፋ፣ ሀብታሙ ሰጠኝ፣ ሐሩት ፍቅሬ፣ምዛርት ትግስቱ፣ ኩብንሽ ብርሃኑ፣ ግርማ በቀለ፣ ኑብዩ በቀለ፣ አስጢፋኖስ አበራ፣ ወ/ሮ ፋንቱ አራማየሁ፤

በተለይ

- ለስለሺ ሀነስ
- ለራኒ ዮሐንስ
- ለአስቻለው ፍሴሐ

ለአደረጋችሁልኝ መልካም ነገር ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

- ረቂቁን በማንበብ ገንቢ አስተያየታችሁን ስለሰጣችሁኝ
  - ለደራሲ እንዳለጌታ ከበደ
  - ለደራሲ ልዑል ግርማ
  - ለጋዜጠኛ ራኒ ዮሀንስ
  - ለጋዜጠኛ እናኒያ ሶሬ
  - ለጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩ

ከውዱ ጊዜአችሁ ላይ ቀንሳችሁ ሰጥታችሁኛልና እጅግ በጣም አመሰግናለሁ::

- በአጠቃላይ በሁሉ እንቅስቃሴዬ ውስጥ ድጋፋችሁ ላልተለየኝ ሁሉ ስማችሁን ዘርዝሬ አልወጣውም እና ምስጋናዬ የከበረ ነው ::

## ማስታወሻነቱ

ለሚሚ

@BOOKALEM

# ምዕራፍ አንድ

## -1-

## 1996 ዓ.ም

ህዳር

ሐሙስ

ከምሽቱ 2:45

ቦታው አዲስ አበባ በተለምዶ አምስት ኪሎ ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ሙዚየም ጀርባ ከሚገኙት ጥንታዊ መንደሮች አንድ ትልቅ መኖሪያ ቤት ግቢ ውስጥ ነው። ግቢው ሰፊ ከመሆኑ ባሻገር በትላልቅ የዘግባና የፅድ ዛፎች ተሞልቷል። ውስጡ ባለአንድ ፎቅ ጥንታዊ ቤት ይገኛል። ቤቱ ረጅም ዕድሜ እንዳስቆጠረ ያስታውቃል። ይሁን እንጂ ውብቱን አላጣም።



Cover Design ertale art studio

አከፋፋይ:- ሲትማን ጀኔራል ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር
አድራሻ:- ጥቁር አንበሳ ፪ኛ ደረጃ ት/ቤት ፊት ለፊት ትራኮን ሕንጻ
ስልክ 0911899468/0111262021
ETAFZER PRINTERS

40 ብር

@BOOKALEM